ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ ነሐሴ 1 ቀን 2018 ዓ.ም

# ፍልሰታ የትኩረት ወቀት

በዚህ ወቅት በአገራችን በኢትዮጵያ  እንስሣት እንደወትሮው ቀን ተረጋግተው ሳር አይነጩም። ሌሊትም በበረታቸው ሆነው እንደ ሰላሙ ጊዜ  ሳር አያመነዥኩም። በዚህ ወቅት ከድንጋይ በቀር ከመሬት ክፍ ብለው በክንፋቸው የሚበሩ በምድር በእግር የሚሽከረከሩ ሁሉ እየተፈናቀሉ በመጨነቅ ላይ ናቸው። በሚተኮሰው ጥይት በሚሰሙት ጫጫታ እየበረገጉ ናቸው።  በዚህ ወቅት ከቋጥኝ ድንጋዮች በቀር በኢትዮጵያ ውስጥ የማይጨነቅ የማይበረግግ ፍጥረት የለም።

ምንም እንኳ ወያኔወች ድንበር እያፈረሱ ሕዝቡን በዘር ከፋፍለው ኢትዮጵያውያንን በታትነው ኢትዮጵያን ከተቆጣጠሩበት ጊዜ ጀምሮ ከረሳ ምቾት ፈላጊወች በቀር ሰባዊነ ስሜት ያላቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያን ያረፉበት የሰላም እንቅልፍ ነበራቸው ባልልም፤ ብልጽግና በሚል ስም ራሱን አደራጅቶ ኢትዮጵያን ከተቆጣጠርበ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዚህች ቅጽበት ድረስ በኦርቶዶክሳውያን ላይ እየነደደ ያለው እሳት ለንጽጽር የሚጠቀስ ወደር የሌለው ከመከራ ሁሉ የባሰና በእጅጉ የከፋ ነው።

ከአማራውና ከኦርቶዶክስ ክርስትና ጋራ ንክኪ ያለው ሁሉ እየተመረጠ በሚጨፈጨፍበት ባሁኑ ወቅት፡ የቆየ ቂምና በቀል ያላቸው የሚደርሰው መከራ ሠርግና መልስ የሆነላቸው ሰወች ሊሸፍኑት ቢጥሩም እጅግ ጎልቶ ዓለም እየተመለከተው ስለሆነ ሊደብቁት አልቻሉም። ሕዝቡ ራሱን እንዳይከላከል ለማፍዘዝ የባሰ ይመጣልና አሁን የሚደርስባችሁን መከራ ቻሉት የሚሉት ጫጫታ ደምቆ እየተሰማ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላሙ ጊዜ ከነበረው ባህርዩና ቦታ ሳይንቀሳቀስ በሰላም ጊዜ እንደነበረው እንደ ቋጥኝ ድንጋይ ተጎልቶ የሚታየ ማነው ብየ ስፈልግ እኔን የመሰሉ ቄሶች ብቻ መሰሉኝ። ይህች የፍልስታ ሳምንት የማያርፈውን ሐሊናችንን የምንፈትሽባት የተለየች የሰባዔ ወቅት ናትና ከዚህ ጫጫታ ውስጥ ራሴን ፈልጌ ለማግኘት ከራሴ ሐሊና ጋራ መታገል ጀመርኩ። ከወጭም ከውስጥም በሚነፍሰው የሀሳብ ከሚያንገላታው ሰው አንዱ እንደመሆኔ ከኢትዮጵያና ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያ  ብዙ የተለያዩ የሐሳብ ማእበላት ወደኔ እየጎረፉ ሐሊናየን አጥለቀለቁት።

ካጥለቀለቁኝ ሐሳቦች በብዙ ትግል ራሴን መንጭቄ በፍልስታ ወቅት በንባብ በትርጓሜና በዜማ ወደ ሚደመጡት ምንባባት አተኮርኩ። አባ ሕርያቆስ በድርሰታቸው “ወሶበ እሔሊ ዘንተ ይፈቅድ ሐሊናየ  ይጸአን መትከፈ ነፋሳት ወይስርር ምሥራቀ ወምዕራበ ሰሜነ ወደቡበ  ወውስተ ኩሉ አጽናፍ ይርአይ ሕላዌሆሙ ለፍጡራን ወይመጥን ዕመቃቲሆሙ ለአብሕርት ያእምር ሉዓሊሁ ለሰማይ ወየአይይ እንተ በኩለሄ ይሰእን ወይግባዕ ኀበ ዘታካት ሕላዌሁ”  (ቁ 86) ብለው በተናገሩት ላይ ትኩረቴን አንተራስኩት። ይህም ማለት፡- እንዴተኛ ተፈጥሮ የማይፈቅድለት ሐሊናየ  ወደ ምሥራቅ ወደ ም ዕራብ ወደ ሰሜን ወደ ደቡብ በረረ። ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የፍጡራንን ሁኔታ ፈተሸኩ፡፡ የባህሮችን የወንዞችን ጥልቀታቸውን ስፋታቸውንና በውስጣቸው የሚተራመሱትን ፍጥረታት  እየሁና ሐሊናየ ወደቀደመ ሐሳቡ ተመለሰ” ነው የሚሉት። እባ ሕርያቆስ እንዳሉት የኔም ሐሊና ከምኖርበት ካሜሪካ እየተነሳ በምስራቅ በምዕራብ በሰሜን በደቡብ ያለው ሰው የሚያሰማውን ዋይታ ከቃኘሁ በኋል ወደተወለድኩበት ወደ ኢትዮጵያ ምድር ወዳደኩባት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ዋይታና ሰቆቃው ተመለሰ።  የቀደሙ ሊቃውንት አበው በዘመናቸው ያካባቢያቸውን ሁኔታ የተረጎሙበትን አንድምታ የዘመናችን ሰወች አምመው ጠምጥመው ለመተርጎም ሲታትሩ ተመለኩትኩ። “የሰማዩን ፊትማ መለየት ታውቃለህ የዘመኑን ምልክት መለየት እንዴት አትችሉም? “ማቴ 16፡3” ብሎ የተናገረው የጌታችን ተግሳጽ ትዝ አለኝ ። በዚህ ወቅት ከድንጋይ በቀር ከመሬት ክፍ ብለው በክንፋቸው የሚበሩ በምድር በእግር የሚሽከረከሩ ሁሉ እየተፈናቀሉ በመጨነቅ ላይ ናቸው። በሚተኮሰው ጥይት በሚሰሙት ጫጫታ እየበረገጉ ናቸው።  በዚህ ወቅት ከቋጥኝ ድንጋዮች በቀር በኢትዮጵያ ውስጥ የማይጨነቅ የማይበረግግ ፍጥረት የለም። ገዳማት እየተቃጠሉ መነኮሳት እየተገደሉ ባሉበት ወቅት፡- የድሮ አባቶችንን ለምምሰል  በሰላሙ ጊዜ አባቶቻችን ያደርጉት የነበረውን አንድምታ አምመው ጠምጥመው የሚያነበንቡት ቄሶች ምን አይነት ህሊና አላቸው? የት ነው ያሉት። በዘመናቸው የሚያነበንቡትን አንድምታ ያዋቀሩት ሊቃውንት ቀና ብለው ቢሰሟቸው “የሰማዩን ፊትማ መለየት ታውቃለህ የዘመኑን ምልክት መለየት እንዴት አትችሉም? “ማቴ 16፡3” በሚለው በጌታችን በመድኃኒታችን ተግሳጽ መገሰጻቸውን እንዴት አያውቁም? የሚል ጥያቄ ሐሊናየን ወረረው።

እነዚህን አስመሳይና ግዴለሾች  ቀሳውስት “ዘይትሐጸብ እምድሕረ ገሥሦ በድነወ ወካዕበ ይደግም ገሢሦ ምንተ ይበቁዖ ተሐጽቦ፡ ከማሁ ሰብእ ዘይጸውም  እንበነ ኃጢአቱ። ወካዕበ የሐውር ዳግመ የአብስ ። መኑ እንከ ይሰምዖ ጸሎቶ። ወምንተ ይበቁዖ አሕምሞ ነፍሱ”(ሲራ 31፡31) በሚለው ምንባብ ስፈትሻቸው፡- በመቃጠል ላይ ያለው ሕዝበ ክርስቲያን እንኳን የአንድምታ ንብናቦቻቸውን ቅዳሴያቸውን ሰምቶ አሜን የሚል አልመሰለኝም። ይህም ማለት፡-የሞተ በድን የነካ ሰው እጁን ከታጠበ በኋል መልሶ ለሚነካ ሰው ቀድሞ መታጠቡ እንደማይጠቅመው በግብር በሕሊና የቆሸሸ ሰው ጸሎቱ ምን ይጠቅመዋል” ማንስ ይሰማዋል? ማለት ነው።  እነዚህ ቀሳውስት ኑሮ ተመችቷቸዋል። የህዝቡን ጭንቀት አያዩም ዋይታውን አይሰሙም የነሱን አንድምታ መነው የሚሰማቸው? ።

ባንድ ወቅት Joseph Goldstiein የሚባሉ “mindfulness a practice  guide to awakning”  በሚል ርእስ የተጻፈ መጽሐፍ ላይ ያነበኩት ትዝ አለኝ ። ይህ መጽሐፍ የሚገልጸው በፍልሰታ ከሚደረገው ትኩረት ጋራ የተገናኘ ነው። “Being mindful internally, externally and both reminds us of the comprehensive nature of mindfulness practice to be aware of whatever  there is, whether it is within us or without. And in the end, to go beyond this division altogether.”(29) ይላል። ይህም ማለት ከውስጥና ከጭ ስለሚነፍሱት የሀሳብ ማእበላት ሁሉ ባካባቢ ያሉትን ፍጥረታት እንድንረዳ የሚያግዙ መሆናቸውን ያሳይና ሁሉም  ከመከፋፈል  አልፈው የሚገናኙበት አንኳር እንዳለ ያሳያል። ክርስቶስ የተናገረውን ተግሳጽና የአባ ሕርያቆስን ንግግር ከጎልድስቲን ንግግር ጋራ ደምሬ እኛ ቄሶች ሌሊት እየመላለስን ወደ እምናንጎራጉረው ወደ ጋስጫው ወደ አባ ጊዮርጊስ ድርሳን ተመለስኩ።

“ንዒ ኀቤየ ኦድንግል ምስለ አናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል  ትእዛዘ ንጉሥ ዘዐበዩ  ለአምላከ ሰማይ  ዘገነዩ ማእከለ እሳት ዘጸለዩ” የሚለው ላይ ሐሊናይ ተቀረቀረ። አናንያ አዛርያና ሚሳኤል ከአገዛዙ የሚወጣውን ጸረሰብ  ትእዛዝ  ወርውረው በህዝብ ላይ በሚነደው እሳት መካከል ገብተው ድምጻቸውን ለፈጣሪና ለፍጡር አሰሙ” የሚል ነው። አባ ጊዮርጊስ ለምን ጻፉት? ለማን ጻፉት? ዜማ ለብሶ እንድናንጎራጉረው ለምን ተደረገ? በሚል ጥያቄ  ራሴን አስጨነኩት። ለዚህ መልስ ሳላገኝ፡ ካንድ ዛፍ ጫፍ ወደ ሌላ ዛፍ ጫፍ እንደሚዘል ጦጣ አባ ጊዮርጊስ “ንዒ ኀቤየ ኦድንግል ምስለ ምስለ ወልድኪ ፍቁርኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ትባርኪ ላዕሌነ” ብለው ወደጻፉት ሐሊናየ ተንጠለጠለ። ይህም  “ድንግል ሆይ ትባርኪን ዘንድ ከልጅሽ ከወዳጅሽ ጋራ ደረሽልን” ማለት ነው። የወሎው አባ ሕርያቆስ በዚህ ወቅት ባካባያቸው ከደረሰው መከራ ምን ገጥሟቸው ነው ይህን የድረሽልን ተማህጽኖ ያሰሙት? ብየ ራሴን ጠየኩት። ወሎ ላይ ያሉት የድሮ የአያ መርሐ ጽድቅ ያሁን የአቡነ ቄርሎስን ምሬት ሰማሁ። የልጃቸውን የአቡነ ኤርምያስንም ጭንቀት አዳመጥኩ።

ነጭ ለብሰው በወርቅ ወንበር ላይ ተቀምጠው አንድምታ ከሚያሰሙት የደብር አለቆች ጋራ የሲኖዶሱ ጸሐፊ የአቡነ ዲዮስቆሮስንና የስራ አስሊያጁን የአቡነ  ሳዊሮስን የመዝናናት ኑሮ ተመለከትኩ። ርኅርኂተ ሐሊና እመቤታችን **“እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል በክንዱ ኃይል አድርጓል።** ትዕቢተኞችን በልባቸው ሐሳብ በትኗል። ገዥወችን ከዙፋናቸው አዋርዷል። ትሑታንንም ከፍ አድርጓል። የተራቡትን በበረከቱ አጠገባቸው ባለጠጎችንም ባዷቸውን ስዷቸዋል”(ሉቃስ 1፡50_55)።  ብላ የተናገረችው ቃል ትውስ አለኝ። እመቤታችን የተናገረችውን በተማርኩት አንድምታ ፈሊጥ ስመረምረው፡ ክርስቶስን በጸነሰችበት ወቅት የተናገረችው ስሜቷን የገለጠችበት መግለጫ (መፈክር) እንጅ ጸሎት አይደለም። ታዲያ የኛ አባቶች ለምን እንዲጠቅመን ነው በክርስቲያኑ ዓለም ያልተደረገ ልማድ ለኛ ለልጆቻቸው ብቻ  በመከራችን ጊዜ ሁሉና የየእለቱ ጸሎታችን መግቢያ አድርገን እንድንደግመው የሰሩልን? በተለይ   **“እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል በክንዱ ኃይል አድርጓል”** የምትለው ሐረግ ለኛ ምን ትጠቁመናለች ብየ አሰላሰልኩ። የእመቤታችንን መፈክር በጸሎት መልክ እንድንደግመው የሰሩልን አባቶች፡ ኢትዮጵያን ተግዳሮቶች በገጠሟት ዘመን ሁሉ ያሻገረችባቸውን እሴቶች እስከ ትውልድና ትውልድ እንድናስቀጥል ለማስገንዘብ መሰለኝ።

እረፍት የለሹ ሕሊናየ፡- ቅድስት ድንግል ማርያም "እስከ ትውልድና ትውልድ" ብላ ከገለጸቻት አከስገንዛቤ ሀሳብ ነጥሮ "ንዒ ኀቤየ አድንግል ምስለ አናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ትእዛዘ ንጉሥ ዘዐበዩ ለአምላከ ሰማይ ዘገነዩ ማእከለ እሳት ዘጸለዩ" ወደሚለው ወደ ወሎው አባ ጊዮርጊስ እንጉርጉሮና ትካዜ ተመለሰ። ገ/ኢየሱስ እስከ ፓትርያርክ ቴወፍሎስ ከዚያም በዘመናችን በህዝብ ላይ ወደሚነደው እሳት እንደ አናንያ አዛርያና ሚሳኤል እራስቸው እየወረወሩ ለትውልድ ያስተላለፏቸውን እሴቶች ተመለከትኩና ራሴን ጨምሬ በዚህ ዘመን የምንገኘውን ቄሶች በተለይም አንድምታ ተርጓሚወችን ታዘብኩ።

ትዝብቴን በዚህ ዘመን በምንገኘው ቄሶች ላይ ብቻ መግታት አልቻልኩም። መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬም ወደ ውጭ ስለሚላኩ ተማሪወች "ለልጆቻችን እሴቶችን ሳናስተምራቸው ኢትዮጵያን ሳያውቋት አስተምሩልን እያልን ሲተገሉን ወደ ኖሩት ባእድ አገሮች አትላኳቸው። ሳናስተምራቸው መላክ የፈለጉትን እንዲሞሉበት ባዶ ሸክላ እንደመላክ ነው። ተሞልተው ከመጡ ያወቁ እየመሰላቸው እሴቶችን ያፈርሷቸዋል። እሴቶችን ተረድተው ነቅተው በመጠበቅ በሚሰለፉት ልጆቻችን ላይ ሸክም እናከብድባቸዋለን" ብለው የተናገሩት ትዝ አለኝና ባስኳላ ተማሪወች ወገኖቼ ላይም ትዝብቴ እጽፍ ድርብ ሆነ። ከሁሉም "የሰማዩን ፊትማ መለየት ታውቃለህ የዘመኑን ምልክት መለየት እንዴት አትችሉም? "ማቴ 16፡3" በሚለውን በጌታችን መመድኃኒታችን ተግሳጽ ራሳቸውን መፈተሽ ካቃታቸውና አባቶቻችን ያወረሱንን እሴቶች መመስከር ከተሳናቸው፡ ነገር ግን ሁሉንም እናውቃለን ከሚሉ ከዘመናችን ሊቃውንት ራሴን ለማግሸሽ እየተገደድኩ ነው።

## በሁሉም የተረሱትና ሁሉም የዘመተባቸው እሴቶች ምን ነበሩ?

ወያኔወች ሊበታትኗት የነበርችው ኢትዮጵያ ባሁኑ ወቅት ስሟ ተደጋግሞ ቢጠራም ለመፍረስ ስጋት ላይ በመሆኗ እንዳትፈርስ ለመገንባት 4ሽ የምክክር ጉባኤ ተሰብስቦ እየተረባረበ ነው የሚል ተዳድግሞ ሲነገር እሰማለሁ። 4ሽ የምክክር ጉባኤ ተሰብስቦ በመነጋገር ላይ ቢሆንም፡ በትረ መንግሥቱን የጨበጠው አካል የራሱን አፍራሽ እቅድ ለማሻገር ኃይሉን እንዲያጠናክሩለት ሌሎች የድምጽ አዳማቂወች በስውር ሰብስቦ ወደ ጉባኤው እያስገባ ነው የሚል አጋላጭ ድምጽ በሰፊው እየተሰማ ነው። ከጉባዔው እያፈተለኩ በጭምጭምታ ይነገሩ የነበሩት አደገኛ አፍራሽ ሐሳቦችን የጉባኤው መሪወች ለማፈን ቢጥሩም በመጨረሻ ራሳቸው መሪወቹ አመቻማች በሆነ ፈሊጥ መሹለኪያ ንግግሮችን ሲናገሩ በመሰማት ላይ ናቸው። ከ 4 ሽ ሌላ ከመጀመሪያው ያልነበሩ በስውር መክተቱ ኢትዮጵያ የምትገነባባቸውን እሴቶች ወደጎድን ገሸሽ አርጎ የሚከፋፍል ሐሳብ ለመክተት እንዳለው ጥርጥሩን ወደ አማናዊነት የሚያሸጋግር ነው።

"ሕዝባዊ ያስተሐምም በነፍሱ አንተሰ ጸርከ ጸረ ከቡደ"(ፍ ነ አ 5፡120) በሚለው ቀኖናዋ ቤተ ክርስቲያናችን እንደምታስጠነቅቀው፡- 4 ሺ ይቅርና 120 ሚሊዮንም ቢሆን በየግሉ ኑሮ ውጥረት ላይና ከየ አቅጣጫው በሚወረወርበት አወናባጅ ወቅት ላይ ያለ ሕዝብ በስውር ደባ ተጠቅልሎ የቀረበውን ጎጅ ሀሳብ በተመሳሳይ ፍጥነት ያየዋል ተብሎ አይታሰብም። ተቆላልፎ በቀረበው የሴራ ፖለቲካ ተጠቅልሎ የቀረበውን ተንኮል መረዳት የሚችሉት፡ ሱባያቸውን (ጸሎታቸውን) በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የመሠረቱ ኃያልን የሚባሉት መንፈስ ቅዱስ የገለጸላቸው ናቸው። ወይም የተማሩ የሚመራመሩ ታሪክን ከታሪክ፡ ትውልድን ከትውልድ የሚያነጻጽሩና በፖለቲከኞች የሴራ ጥልፍልፍ ውስጥ ያለውን አደገኛ ሴራ ለመረዳት የሚጥሩ ናቸው። ኢትዮጵያን በዓለም ልዩ ያደረጓት በጨለማው ዘመን የነበሩ የጥንቶቹ ጥቂት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ከውጭ ጠላት እየታገሉ ኢትዮጵያን ከተቆራረሰችበት ሕብረተሰቡን ከተበታተነበት እየመለሱ ያዋቀሩባቸው ባብነቱ ቅኔ ትምህርት የቀመሯቸው እሴቶች ነው።

ኢትዮጵያን ፈርሳ እንደገና መገንባት ባስፈለጋት በዚህ ዘመን ያሉ ሊቃውንት እንደ ከቀደሙ ሊቃውንት ጥበብ አመንጭተው በፍቅር ሊገነቧት ይቅርና፡ የቀደሙ አባቶቻችን በቅርስነት ያስቀመጡልንን መገንብያ እሴቶች ፈልገው ማግኘት አለመቻላቸው አባቶቻችንን እንዲደነቁ ያድርጋቸዋል። ከአባቶቻን እንሻላለን እያሉ የነቀፏቸውንም ሁሉ እንዲሸማቀቁ አድርጓቸዋል። የቀደሙ አባቶቻችን በቅርስነት ያስቀመጡልንን መገንብያ እሴቶች የቀረጹባቸውን ቅኔወችና እንዴት ሕዝባውያን አድርገው በህዝቡ ጭንቅላት እንዳሰረጿቸው በሁለት ከፍየ ለማሳየት ከሞከርኩ በኋል ተማርን ብለው በህዝቡ ፊት ለሚቆሙት የዘመኑ ሊቃውንት በማቀርበው ጥያቄ እደመድማለሁ።

## የቀደሙ አባቶች ሊቃውንት ኢትዮጵያ እንዳትፈርስ ሕብረተሰቡ እንዳይበተን ያዋቀሩባቸው እሴቶች በግእዙ ቅኔ

የውጭ ጠላት ሲመጣ መጀመሪያ የሚዘምቱባቸው እሴቶችን ባዋቀረው አካልና ከእሴቶቹ ጋራ በተጣበቀው ሕብረተ ሰብ ላይ ነው። እሴቶችን በግዕዙ ቅኔ ያዋቀረችው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። እሴቶች የተዋቀረቡት አካል መላው ሕብረተ ሰብ ቢሆንም፡ እሴቶችን በቀላሉ የማይለቃቸውና ተላልፎ የሚሞትለታቸው አካል ማእከላዊው ሕዝብ ነው። ቀጥሎ የሴቶችን ሰንሰለቶች መበጣጠስ ነው። በመጨረሻ በቀላሉ የተታለለላቸውን ሕዝብ ኢትዮጵያዊነቱን ያስረሱታል። ባለቤትነቱን ባለ አገርነቱን ከሕሊናው ይገፉታል። ለኢትዮጵያ ባለቤት አይደለሁም። ባለ አገር አይደለሁም። የሚል የባይታወርነት ስሜት ያሰርጹበታል። ከእሴቶች ጋር ጥብቅ ትስስር አለው ብለው በሚገምቱት ሕብረተ ሰብ ላይ የቀረውን ሕብረተ ሰብ ያዘምቱበታል።

የእያንዳንዱ ዜጋ አካል ከሌላው ዜጋ አካልና ከኢትዮጵያ ምድር ጋራ የተሳሰሩባቸው እሴቶች ማንም ሰው በሳይንሱ ዘልቆ ካልተማረ በቀር፡ የተሸከመውን የልቡን አገልግሎት እንደማያውቅ ቅኔ ቆጥሮ መቀኘት የሚችል ሁሉ በቀላሉ የሚረዳቸው አይደሉም። በኋላ እንደምናየው ሊቃውንቱ ማንም ሰው በቀላሉ ከማይረዳው ከግእዙ ቅኔ ውስጥ ፈልቅቀው ሕዝባውያን በማድረግ በዜጋው ሕሊና አስርጸዋቸዋል። በዜጋው ሕሊና ያሰረጹባቸው እሴቶች ከየት እንደ ወሰዷቸው ለማሳየት ያብነቱን ባጭሩ ካሳየሁ በኋል፡- በግእዙ ተቀርጸው የተቀመጡትን ቅርሶች ለመረዳት ከኮፌዳዋ ጀምረን ቢያንስ የጉባኤ ቃናንና የመወድሱን ይዘት እንመለከታለን።

## ኮፌዳ

ኮፌዳ ከሰሌን ወይም ከቄጠማ የምትሰራ ናት። ከየመንደሩ እየዞርን በመለመን የምንሰበሰበውን ምግብ እንይዝባታለን። ከህብረተ ሰቡ የምንሰበስበው ልዩ ልዩ ምግብ ወደ ዚህች ኮፌዳ ሲገባ ስሙ ተለውጦ ውጥንቅጥ ይባላል። ከህዝብ የተሰበሰበው ውጥንቅጥ የተባለው ምግብና፡ የመግቡ መያዣ ኮፌዳ ለሰምና ወርቅ ቅኔ ትምህርታችን መሰረቶች ናቸው። ከሕዝብ የተሰበሰበው ውጥንቅጥ የተባለው ምግብ እና ኮፌዳዋ በሰምነት ያገለግላሉ። ከህዝብ የተሰበሰበው ውጥንቅጥ የተባለው ምግብ ሰም ሲሆን፡ የምግባችን ምንጭ የሆነው ሕዝብ ወርቅ በመሆን ያገልግላል። ውጥንቅጥ የተባለውን ከህዝብ የተሰበሰበውን ምግብ ሰብስባ የምትይዘው ኮፌዳዋ ሰም ስትሆን፡ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለውን ሕዝብ ሰብስባ የያዘችው ኢትዮጵያ ወርቅ ትሆናለች።

ኮፌዳዋ በአይጥ ብትቀደድ በውስጧ የተሰበሰበው ውጥንቅጥ ይበተናልና ለኮፌዳዋ እንድንጠነቀቅ አይጥ ከማይደርስባት ቦታ እንድናስቀምጣት ያብነቱ መምህራን በጥብቅ ያስጠነቅቃሉ። ምሥጢሩ የሚያተኩረው በሰሙ ላይ ሳይሆን በወርቁ ላይ ነው። ወርቁ ሕብረተ ሰቡና ኢትዮጵያ ናቸው። ኮፌዳው ብትቀደድ በውስጡ ያለው ውጥንቅጥ እንደሚበተን የኢትዮጵያ ዳር ድንበር በአይጥ (ወራሪወች)ቢደፈር (ቢቀደድ) ሕዝቡ ይበተናል። ስለዚህ ለኮፌዳዋ የሚደረገው ጥንቃቄ ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር የሚደረገውን ጥንቃቄ የሚያመለክት ነው። ለውጥንቅጡ የሚደረገው ጥንቃቄ ለሕዝቡ አንድነት የሚደረገውን ጥንቃቄ የሚያሳይ ነው። ውጥንቅጥ ሌላ ሕዝባዊ ይዘት አላት። ወደ ጥልቅ ይዘቷ ስንገባ ውጥንቅጥ ማለት መወናቀጥ መቀላቀል መደባለቅ ሲሆን ሌላው ትርጉሟ ውጥን ና ቅጥ ማለት ይሆንና ከጅምሩ ቀጥ ያለ ትውልድ ማለትም ይሆናል። ከዚህ ቀጥየ አቅሜ ቢፈቅድልኝ ወደ ቅኔው ጥልቀት በመሻገር ኢትዮጵያ የተጠበቀችባቸውን እሴቶች ከጉባዔ ቃና በመጀመር እንዴት እንደተዋቀሩ ለማሳየት እሞክራለሁ።

## ጉባዔ ቃና

"በጥንታዊት ኦርቶዶክስ ስርአታችን ይህን የመሰለ ለትውልድ የሚተላለፍ ዓቢይ ነገር ሲነገር በወቅቱ ከተከሰቱት ቢያንስ አንዷን ክስተት በግእዙ ቅኔ መጥቀስ ተገቢ ነው። በግእዙ ቅኔ ቢጀመር ቅርሳዊነቱን ያጠነክረዋል" ይላሉ መምህራን አባቶች ። በዚህ ወቅት የሚጠቀሱ ብዙ ታሪካውያን ክስተቶች ቢኖሩም፤ ለዚህች ጦማርና ለራሴ ተልእኮ ቀራቢ የሚሆነው በዚህ ዘመን በተቋቋመው በሃይማኖቶች ድርጅት የተከሰተው ነው። በዚህ ዘመን ለተመሰረተው ለሃይማኖቶች ስብስብ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ ተብለው የተሰየሙት ቄስ ታጋይ የሚባሉት ናቸው። ቄስ ታጋይ ተወክለው ይህን ከባድ ሐላፊነት የተቀበሉት ባንድ ወቅት ጠ/ምንስቴሩ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችንን አገርነት ናት ላሏት ቤተ ክርስቲያን ነው። ፡ይህን

ከባድ ሐላፊነት ተቀበለው እንዲገቡ ማነው የወከላቸው? በምን ብቃታቸው ገቡ? የተወገዱበት ምክንያትስ ምንድነው? ማነው ተጠያቂው? ለተፈጠረው ችግር የሳቸው መወገድ መፍትሔ ይሆናል? ወይስ በእሳቸው የተከሰተው ጥፋት እሳቸውን ብቻ የሚመለከት ነው? ቅኔአችን በተዋቀረችባት ወቅት ከተከሰቱት ብዙ ክስተቶች ለምልክት ያህል አንዷን ማሳየት ተገቢ ስለሆነ በቄስ ታጋይ የተከሰተውን እንደማሳያ አድርጌ በራሴ ቅኔ ለማቅረብ ሞከርኩ፡፡

<u>በቤተ ክህነት ፈድፈደ፤ ወተመከዓበ ጌጋይ፡</u>

<u>አኮኑ ተዘብሀ መስዋዕተ ጣዖት ታጋይ</u>

ለኃጢአት ሥርየት መስዋዕት ሆኖ የሚሰዋ ለሀገር ምሕርት የሚያተርፍ እንከን የሌለበት ነው (ዘሌ 6፡6) ፡፡ ታጋይ ለመስዋዕትነት መቀረብ የማይችል ነቀፋ ያለበት እንክርዳድ ነው፡፡ ያቀረቡት ከቁጣ ከግድያና ከኩብለላ መንፈስ መላቀቅ የማይችሉ ቃኤላውያን ናቸው፡፡ የቃኤል መስዋዕት የበለጠ መከራ በማስከተል ተቅበዝባዥ የሚያደርግ እንጅ ሥርየት የሚያሰጥ አይደለም፡፡ ታጋይ የተባለውም የበደል መስዋዕት ሆኖ መቅረብ የማይችል ነው፡፡ ከገባበት ጀምሮ እስከተወገደባት ቅጽበት በቆየበት ጊዜ ነውር ስርቷል፡፡ ንውሩን ብቻውን አልሠራውም፡፡ ለቦታው ይመጥናል ብሎ ያቀረበውም፡፡ ታጋይን ብቻ በደለኛ አድርጎ ያስወገደ ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያናችን ጋራ ምንም ቀረቤታ ከሌላቸው ከሞርሞኖች ጋራ በነበረው ቅርበት በተሠራው ስህተት ብቻ እንኳ የተካፈሉት ሰወች ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ለቀረበበት ወቀሳ በሲኖዶሱ ውስጥ ያሉት በህዝብ ላይ የሚደርሰውን በደል ዘውር ብለው እንደማያዩትና እሱ ይልቅ የተሻለ ሥራ እንደሠራ የተናገረውን ስምቻለሁ፡ እሱን ብቻ መስዋዕት ማድረግ ተቀባይነት የለውም፡፡ በታጋይ የተወሰደው ርምጃ ለሃይማኖት ተቋማትም ሆነ ለወከለው ቤተ ክህነት ሽፋን እንጅ ለኢትዮጵያ የሚጠቅመው ፈውስ የለም፡፡ እንደ መግቢያ ያቀረብኳት ቅኔ በወቅቱ የተካሄደውን ታሪክ በመጥቀስ ወቅቱን ለማሳየት ጠቀስኩት እንጅ ይዚህች ጦማር አላማ ሊቃውንት አበው በቅኔው ውስጥ በቅርስነት ያዋቀሯቸውን ፈሊጦች ለማሳየት ነው፡፡

ከላይ ያቀረብኳት ጉባዔ ቃና ቅኔ አራት ስንኞች ሁሉት በግጥም የተገናኙ ሐረጎች አሏት፡፡ በሐረግ በግጥም ያልተደራጀ ስነ ጽሑፍ <u>ስድ ንባብ</u> ይባላል፡፡ በትዳር ሳይገጥም በላጤነት መኖርን ያመለክታል፡፡ አራቱ ስንኞች ሁለቱ ሐረጎች በተመሳሳይ ፊደል ቃላት ይገጥማሉ፡፡ ቤት ይመታሉ፡፡ በገጥም ቤት መምቻዋ ፊደል ይ ናት የመጀመሪወቹ ሁለቱ ሐረጎች በይ ፊደል የምታልቀው ጌጋይ ናት፡፡ ተከታዮቹ ሁለቱ ሐረጎችም መስዋዕት በሆነው በይፊደል ያለቀችው የቄስ ታጋይ ስም ናት ፡፡ <u>በአራት ስንኞች በሁለት ሐረጎች ተጋጥማ የተዋቀረችውን ቅኔ ከዚህ በታች እንደዚህ አስቀምጫታለሁ፡፡</u>

<u>የመጀመሪያዋ ሐረግ "በቤተ ክህነት ፈድፈደ፤ ወተመከዓበ ጌጋይ" የምትለው ከዚህ በታች እንደተገለጸው በሁለት ስንኞች የተዋቀረች ናት፡፡</u>

1ኛው ስንኝ "በቤተ ክህነት ፈድፈደ" የምትለዋ ናት፡፡

2ኛዋ ስንኝ "ወተመከዓበ ጌጋይ፡ የምትለዋ ናት፡፡

የመጀመሪያወቹ ሁለቱ ስንኞች <u>"በቤተ ክህነት ፈድፈደ፤ ወተመከዓበ ጌጋይ" ተብለው በመነበብ የመጀመሪያዋን ሐረግ ይሰራሉ፡፡</u>

ቀጣዮቹ<u>ሁ ሁለተኛወች ስንኞች "አኮኑ ተዘብሀ መስዋዕተ ጣዖት ታጋይ" ተብለው በመነበብ ሁለተኛዋን ሐረግ ይሰራሉ፡፡</u>

4 ቱ ስንኞች በሁለት ሐረግነት ተደምረው በይ ፊደል በሚያልቁት በጌጋይና በታጋይ ተጋጥመዋል፡፡ ቤት መተዋል፡፡ የመጀመሪዋ ሐረግ ከሁለት ወላጆቿ ማለትም ከናቷና ካባቷ ተወልዳ ሁለት የትውልድ ስንኞች ይዛ ከሁለት የተገኘ ሐረግ ይዛለች፡፡ ይህች ሐረግ ከሁለት አካላት ከወንድና ከሴት የተገኘውን ባልን ትወክላለች፡፡ ሁለተኛዋ ሐረግም ከሁለት ወላጆቿ (ስንኞች)ማለትም ከናቷና ካባቷ ተወልዳ የትውልድ ሐረግ ይዛለች፡፡ ሚስትን ትወክላለች፡፡ ሁሉት ባልና ሚስት በጋብቻ የየራሳቸውን ስንኞች ይዘው የየራሳቸውን ሁለት ሐረጎች በመደመር ይገጥማሉ፡፡ ቤት ይመታሉ፡፡ ከነሱ የሚወለዱት ልጆች አራቱን ስንኞች ሁለቱን ሐረጎች ማለትም አራቱን አያቶቻቸውን ይዘው ይወለዱና ሕብር ያደርጋሉ፡፡ የአራቱን አያቶች ይዘው የሚወለዱ ልጆች የአራቱ አያቶቻቸውን ስንኞች ሲከተሉ የተቀላቀለ ሰውነት (ድም )ይገኝባቸዋል፡፡ አራት አያቶችን ሁለት ሐረጎችን ይዘው በመጋባት የምተመሠረተው ቤት ወይም ትዳር ለጠቅላላው ለትልቁ ሕብረተ ርስብ (ኢትዮጵያዊነት)መሠረት ናት፡፡ አሁን የ ሰፊውን ሕብረተሰብ ትስስር ወደ ሚገልጸው መወድስ ወደ ሚባለው ቅኔ እሻገራለሁ፡፡

## <u>መወድስ</u>

በቤተ ክርስቲያናችን ሁለት አይነት መወድሶች ስላሉ ልዩነታቸውን መግለጹ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ በቀመር ያልተወሰኑ ከዳዊቱ ተወጣተው በዜማ መልክ ከተቀረጹት እንደ መስታጋብ አርያምንና አርባእትን ከመሳሰሉ ዜማ ትምህርቶች የመሰለል መወድስ የሚባል አለ;፡፡ እኔ የምናገውረው የኢትዮጵያዊነት እሴቶች ስለተቀረጹበት በቅኔው ቤት ስለተማርኩት ስለ መደበኛው መወድስ ቅኔ ነው፡፡ ይህ መወድስ የአራት ጉባኤ ቃናወች ድምር ነው፡፡ ስምንት ሐረጎች አስራ ስድስት ስንኞችን ይዟል፡፡ የዚህ ዐይነት መወድስ ስንኞቹና ሐረጎቹ ቢበዙ እንጅ ከዚያ በታች አይወርዱም፡፡

ከተፈጥሮ ውጭ ትርፍ ጣቶች ብቅ እንደሚሉ አልፎ አልፎ ከመደበኞቹ ወጣ ያሉ ስንኞች ይከሰታሉ፡፡ በአራት ስንኞች በሁለት ሐረጎች የተቀመረችው መወድስ የቤተ ሰብን ውቅር የያዘችውን ያራት ጉባዔ ቃና ድምር ናት፡፡ጉባኤቃና ወደ መወድስ ስትሻገር በስምንት ሐረጎች በ16 ስንኞች በአራት ቤቶች ይቀመራል፡፡ እየሰፋ እየተነካካ እየተጋባ እየተቆላለፈ ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የተሰራጨውን ዜጋ ይገልጻል፡፡ የመወድስ ቅኔ በጉባዔ ቃና የተገለጸውን ሕብረተ ሰባዊ ቀመር አስፍቶ በኢትዮጵያ ምድር የሚኖረው ዜጋ ሁሉ በቅድመ አያቶች ሐረግ እየተሳሰረ በመስፋት ከጽንፍ እስከ ጽንፍ ያለውን ሁሉ ዜጋ በሥጋ በደምና በአጥንት መተሳሰሩን ያሳያል፡ ከዚህ የለሁም የሚል ከኢትዮጵያዊነት የወጣ ነው፡፡

## <u>ሰረዝ</u>

ሰረዝ የምትባለው የቅኔ ዓይነት ከተራ ሰምና ወርቅ ቅኔ ትለያለች፡፡ መደበኛው ሰምና ወርቅ ቅኔ፤ አንድ ወርቅና ወርቁን በምሳሌ የሚገልጽ አንድ ሰም ብቻ ትይዛለች፡፡ ሰርዝ ብዙ ወርቆችንና ብዙ ሰሞችን ደራርባ ስለምትይዝ በቀይ ሽንኩርት ትመሰላለች፡፡ የቀይ ሽንኩርት አካል በተደራረቡ ቅርፍቶች የተሰራ ነው፡፡ ቢላጡ ቢላጡ የሚቆሙት በዚያው በዘሩ ላይ ነው፡፡ ለሽ ዘመን እየተቀንቀሳቀስ እየተጋባና እየተዋለደ የኖረው የእያንዳንዱ ኢትዮጵያውዊ ዜጋን አካል እንደዚህ ቀይ ሽንኩርት የተደራረበ ነው፡፡

አባቶች እንደሚሉት፡-ሰው በፈቃዱ ከተወለደበት ቦታ ርቆ በመሄድ እየተጋባ ከመዋለዱ ውጭ፡ በአኩስም ዘምን ትግራይ ይኖር የነበረው ሕዝብ ከሩቅ ከማእከል ምሥራቅና ከአካባቢዊ አጎራባች አገሮች በከተማዋ ስበት እየተጓተተ ተደባልቆ ይኖር ነበር፡፡ በዮዲት ወረራ አኩስም ስትፈርስ የተደባለቀው ሕዝብ ወደ መላዋ ኢትዮጵያ ተበትኖ በየደረሰበት ያገኘውን እያገባ እየወረሰ ከኖረ በኋላ ከ500 መቶ አመታት በኋላ ግራኛ መሀመድ ከምሥራቅ ተነስቶ ወደ መሐል አገር ሲዘምት ያንኑ ተቀላቅሎ ይኖር የነበረውን ህዝብ መልሶ ገለበጠው፡፡ በየደረሰበት ካገኘው ጋራ እየተጋባ መንደር እየሰራ ኖረ፡፡ በጣሊያን ወረራም መሳፍንቱ እርስ በርስ ሲጋጩ ህዝቡ እየፈለሰ በየደረሰበት እያገባ እየወለደ ኖሯል፡፡ በዚህ ታሪካዊ ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነጠላ ሰምና ወርቅነት አልፎ ድርብርብ ሰምና ወርቅ ሁኗል፡፡ ትግሬው ከአማራው፡ ከፋሩ ከኦሮሞው ከሀድያው ከወላይታው ከሱማሌውና ከቀረው ሕዳጥ ጎሳ ተቀላቅሏል፡፡ አማራውም ከትግሬው ከአፋሩ ከኦሮሞውም ከጉሬውም ከሕድያውም ከሱማሌውና ከቀረው ሕዳጥ ጎሳ ጋራ ተቀላቅሏል፡፡ ሁሉም ተቀላቅሏል፡፡ ሠረዝ የምትባለው ቅኔ ኢትዮጵያውነት በዕሪና (equilibrium) ህብር እያደረገች በቅጽሎች እና በማሰሪያ ግሶች ደራርባ ይዛለች፡፡ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ አካል በዕሪና (equilibrium) የተሰራ ሲሆን ኢትዮጵያዊነት በሰረዝነት እሴቶች ሰንሰለት የተሠራ ነው፡፡ በኮፌዳ በውጥንቅጥና በቅኔ ውስጥ ያሉትን ባብነቱ ትምህርት የተገለጹትን እሴቶች እስከሁን ገልጫለሁ፡፡ ከዚህ በመቀጠል <u>ከብነቱ ትምህርት ተቀድተው ወደ አማረኛ ተገልብጠው</u> ሕዝባውያን ሆነው በህዝቡ የሚገለጹትን ያስኳላው መምህራን የዘመቱባቸውን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ታዛ ሊቃውንት ከሚያስተምሩት ከቅኔው ትምህርት የተቀዱትን ከዚህ በታች ለመግለጽ እሞክራለሁ፡፡

# ከቅኔው የተመዘዙ ሕዝባውያን እሴቶች

ከቅኔው የተመዘዙ ሕዝባውያን እሴቶች አምስት አእማድ ናቸው፡፡ አምስቱ አእምድ በሁለት ፊደላት በተዋቀረች ባለ በምትባለው አገባብ እየተንተራሱ የሚነበቡት አምስት ቁልፍ ቃላት ናቸው፡፡ እነዚህም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፡፡ በነገራችን ላይ እኅታችን ጂጂ ሽባባው

"ቅኑት ባለ ቅኔ ቅኔን የተቀኘው

ወርቁን በሰሙ ላይ ደራርቦ ጋገረው" ብላ ያዜመችውን እሴቶች የገባው አንድ የቅኔ ሰው በጉሮሯዋ ላይ ያስቀመጠላት ይመስላል፡፡ በእህታችን ድምጽ የቀረበው ቅኔ ስለ ቀላጩ ሰም እና ስለ አቅላጩ ወርቅ ለመግለጽ አይደለም፡፡ ደራርበን ስለተሸከምነው ሰውነታችንና ኢትዮጵያ ስትገነባባቸው ስለኖሩት እሴቶች ለመግለጽ ነው፡፡ ወደ አማረኛው እሻገራለሁ፡፡

## ቤት ደም አገር ጋራ አምጣ

ከላይ እንዳልኩት ባለ የምንላት ሁለት ፊደላት አገናዘቢ በመሆን ከላይ ለዘረዘርናቸው ለአምስቱ ቃላት መነሻ ወይም ትራስ በመሆን የህብረተ ሰቡን ትስስር ውህደትና አድነት አምስቱ ቃላት እንዲገልጹ የምታደርግ አገናዛቢ ቁልፍ ናት፡፡ ከቤት እንጀምር፡፡

## ባለ ቤት

ባለቤት ፡- ባለ ከቤት ጋራ ስትጣመር ባለቤት ተበላ ትነበባለች። ቤት ከባለ ተነጥላ ስትነበብ ለመኖሪያ የተሰራችውን ቤት ወይም ህንጻ ትገልጻለች፡፡ ከባለ ጋር ስትጣመር በውስጡ የሚኖሩት ሰወች ለሚኖሩባት ቤት ባለ ቤትነታቸውን ታሳያለች፡፡ ባለቤት ለብዙ ነገሮች መግለጫ ትሆናለች። በባልና ሚስት ጥምረት የሚዋቀረውን ትዳርን ትገልጣለች፡፡ ባል ካንድ መንደር፡ ሚስት ከሌላ መንደር ይመጡና በጋብቻ የጋራ ትዳር ሰምና ወርቅ ሆነው ይመሰርታሉ፡፡ ባልና ሚስት የሚወለዱት ልጆች አባትና እናት በመሆን ከወላጆቻቸው የወረሱትን ሥጋና ደም አጣምረው በማውረስ በልጆቻቸው አማክይነት ከሰምና ወርቅነት ዘልቀው ሕብር ወይም ሠረዝ ይሆናሉ፡፡ ባል ለሚስቱ ባለቤት ነው፡፡ ሚስትም ለባሏ ባለቤት (እመቤት) ናት፡፡ በቤት ውስጥ ላለው ንብረት የተወሀደ አንድ ባለቤትነት አላቸው፡፡ ባል ሚስቱን ባለቤቴ (እመቤቴ ) ይላታል፡፡ ሚስትም ባሏን ባለቤቴ ትለዋለች፡፡ ማነኛውም ዜጋ በተመቼው እየሄደ በየደረሰበት በማግባት ትዳር በመመስረት በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለቤት ነው፡፡ ኢትዮጵያ ቤቱ ናት፡፡ ለመላዋ ኢትዮጵያ ባለቤት ነው፡፡

## ባለ ደም

ባለ ደም፡- አንተ ለኔ የደሜ ባለቤት ነህ፤ እኔ ላንተ የደምህ ባለቤት ነኝ፤ ደምህን እጋራለሁ። ደምህ ደሜ፤ ደሜም ደምህ ነው። እኔ ያላንተ፤ አንተ ያለኔ ህይወት የለንም ማለት ነው፡፡ አስቴር በዳኔ እንዳለችው ያኳላው ትምርት ሲመጣ አንድን ሕብረተ ሰብና ሃይማኖቱን አቤል አደረጎ ደሙ እንዲፈስ አደረገው፡፡ የቀረውን ወደ ቃኤልነት በመለወጥ ደም አፍሳሽ አደረገው፡፡ ትርጉሙ ያልገባው ለማ መገረሳ ወደ ሱስነት ቀይሮ ኢትዮጵያዊነት ሱስ ናት ሲል፡- ትርጉሙ የገባው የጎንደር አማራ የኦሮሞ ደም ደሜ ነው አለ፡፡ የተዘመተበት መከረኛ ሕብረተ ሰብ የባለደምነትን ትርጉም ገለጸው፡፡

## ባለ አገር፡-

ማንም ኢትዮጵያዊ ባንዱት ጎጆ ቢወለድም ለመንደሩ፤ ለአጥቢያው፤ ለወረዳ፤ ለአውራጃውና ለክፍለ አገሩና ለጠቅላላዋ ኢትዮጵያ ባለ አገር እንጅ የተከለለ አልነበረ። ኢትዮጵያ ከዳር እስከዳር አገሩ ነበረች። ባለአገርነት ክብር፤ ኩራት፤ እንጅ ስድብና ኋላቀርነት አልነበረም። አባቶቻችን አተላ ያሉት ለኢትዮጵያዊነት ተቃራኒ ሆኖ ከምዕራቡና ከምሥራቁ ትምህርት ታዝሎ የገባው አስተሳሰብ በዚህ ትውልድ ጭንቅላት እስከሞላበት ዘመን ድረስ፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያ ሁለንተና ባለ አገር ነበር። ያስኳላው ትምህርት ገጠሬውን ያልሰለጠን አድርጎ በመቁጠር ባለአገር የሚለውን ትርጉም በኋላ ቀርነት ተካው፡፡ ያስኳላውን ተማሪ አገር አልባ አደረገው፡፡ የራሱን ባለአገርነት አውልቆ ጥሎ፡፡ ለገጠሬው እንዲሰጥ አደረገው፡
፡

## ባለ ጋራ፡-

ባለ የምንላት አገናዛቢ ጋራ ከምንላት ቃል ጋራ ስትያያዝ በመናበብ ወደ ቃልነት ተለውጣ የሕዝቡን ሰውነት ታገናዝባለች፡፡ ማለትም እያንዳንዱ ደሙን አጥንቱን ሥጋውን ይጋራል ተገናዝቧል፡፡ ይህም የሚያሳየው ሰውነት ደሙንና አጥንቱን የሚጋራና የተገናዘበ መሆኑን ነው፡፡ ትርጉም ተንሸራቶ አቅጣጫውን ሲስት ያንድምታ መተርጉማን ተልእኳቸውን ረሱ፡፡ ያስኳላው መተርጉማን ትርጉሙን በጠላትነት ለወጡት፡፡ ባለጋራ የሚለው ቃል በጠላትነት የመተያየትን መንፈስ አስረጸ፡፡ አሁን የተሰበሰበው 4 ሽ ባስኳላው ተፈናጦ የገባውን አገር አፍራሽ ስሜት ነቃቅሎ ባአባቶቻችን አንድምታ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባለአገርነቱን ከመለሰለት ጀግና ነው፡፡ አለበለዚያ በሰው ሰብሎ ገብቶ የሚንጫጫ የዝንጀሮ ሸንጎ መሆኑ ነው፡፡

## ባለ አንጣ (አምጣ)

ባለ አምጣነትን እያንዳንዱ ዜጋ መመጋገቡን መቀባበሉን መረዳቱን መተጋገዙን መዋዋሱን መወሳሰዱን ያሳያል፡፡ ያበደርኩሁ ያበደርከኝ፤ ያቀበልኩህ ያቀበልኝ፤ ያዋስኩህ ያዋስከኝ፤ የምመልስልህ የምትመልስልኝ፤ የምታመጣልኝ የማመጣልህ ባለ አምጣህ ነኝ፤ ባል አምጣየ ነህ በመባባል አንዱ ከሌላው በደም በሥጋ ባጥንት እና ከሰውነቱ ውጭ ያለውን ሁሉ ለህልውና መሠረት የሆኑትን ቆሳቁሳት መቀባበሉን መጋራቱን የሚያሳይ ነበር፡፡

ኢትዮጵያን ለመገንባት አሁን የተሰበሰበው 4 ሽ ባስኳላው ተፈናጦ የገባውን አገር አፍራሽ ስሜት ነቃቅሎ ከላይ በግዕዙ ባመረኛው ቅኔ በተገለጹት ባአባቶቻችን አንድምታ እሴቶች ኢትዮጵያን መልሶ ካልገነባት በሰው ሰብል ገብቶ የሚንጫጫ የዝንጀሮ ሸንጎ ይሆን? እያልኩ በማሰብ የዘንድሮዋን ፍልሰታ እያሳለፍኳት ነው፡፡ በተረፈ ኢትዮጵያ ስተገነባባቸው በኖሩት ባብነቱ ትምህርት አልፈናል፡ ያስኳላውንም ተምረናል ብላችሁ በህዝቡ ፊት የምትቆሙት የዚህ ዘመን ሊቃውንቶቻችን ሆይ! አባቶቻችን ከሰሯቸው እሴቶች የተሻለ መልስ ካላችሁ ከዚህ ቀጥየ ለማቀርብላችሁ ጥያቄ የምታቀርቡትን መልስ ለማየት እናፍቃለሁ፡፡